# *ወያኔ የትግራይ ህዝብ ተወካይ አይደለም፣*
## *ባይሳ ዋቅወያ*
### *(ለውይይት መነሻ)*

**ክፍል ሁለት (ካለፈው የቀጠለ)**

*ባለፈው ጽሁፌ ባጭሩ ለማስቀመጥ የሞከርኩት የወያኔ መንግሥት በታሪካችን ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በወገኖቻችን ላይ እየፈጸመ ያለው ግፍ ከልክ ያለፈና መደረግ ያልነበረበት ወንጀል መሆኑን እያወቅን፣ ደጋግሞ ስለተነገረን፣ ደጋግመን ስላየነውና ስለሰማነው ብቻ፣ መሆን የነበረበት ነው ብለን መቀበላችን የህሊናችንን መደንዘዝ ያመለክታል ብዬ ነበር። በመሆኑም ከዚህ የህሊና መደነዝ ተላቅቀን ባንድነት በመቆም ህገ መንግሥታዊ መብታችንን ለማስከበር ድምጻችንን እናሰማ ብዬ ነበር የደመደምኩት። በጽሁፉ ውስጥ የወያኔ ገራፊዎች አሰቃዮችና ገዳዮች እንዴት ቢሰለጥኑ ነው እንደዚህ በወገኖቻቸው ላይ ሊጨክኑ የቻሉት የሚል ጥያቄ አንስቼ ነበር። መልስ ጠብቄ ሳይሆን የጭካኔው ደረጃና የግፉ ብዛት ቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔን እንደውጭ ወራሪና ርህራሄ ቢስ አካል አድርጎ ከመቁጠር አልፎ፣ ሀ) ጠቅላላውን የትግራይን ህዝብ እንደ ወያኔ ጨካኝና ርህራሄ ቢስ አድርጎ በመቁጠሩና፣ ለ) ወያኔንም የትግራይ ህዝብ ተወካይ አድርጎ በመፈረጁ፣ አዝማሚያው ወዳልተፈለገ የርስ በርስ ግጭት ማምራት ብቻ ሳይሆን ጥላቻን ባንድ ህዝብ ላይ ያነጣጥራል የሚል ሃሳብ ስላሳደረብኝ፣ ይህንን የተሳሳተ ግምት በጊዜው ለማስተካከልና ወያኔም የትግራይን ህዝብ የማይወክልና የትግራይ ሰፊ ህዝብም ከወያኔ አንዳችም ዓይነት ልዩ ጥቅም ያላገኘ፣ ሰብዓዊ መብቱም ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች እኩል የተረገጠና እንደ ቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ በግለሰብ ደረጃ ጥሩም መጥፎም ሰዎች ያሉበት ማህበረሰብ መሆኑን በተቻለኝ መጠን ለማስረዳት ነው። መሰረታዊው እምነቴ፣ **በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ የግለሰብ እንጂ የህዝብ ጥሩ ወይም መጥፎ የለም የሚለው ነው።***

*ወያኔ በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍና በደል፣ እንኳን እኛ የዓለም አቀፉም ማህበረሰብ ያወቀው ጉዳይ በመሆኑ፣ በደሎቹን ፈጽሟል አልፈጸመም ብሎ መሞገት ጊዜ ማጥፋት ይመስለኛል። ወያኔም ራሱ አልገደልኩም ሳይሆን "የጸጥታ አስከባሪዎቹ ሰላማዊ ሰልፈኞቹን እንዲገድሉ ትዕዛዝ የሰጠሁት ህግና ሥርዓትን ለማስከበር ነው፣ የተወሰደውም እርምጃ ህዝቡ ያሳይ ከነበረው የማስፈራራት ድርጊት ጋር ተመጣጣኝ ነበር" ነው የሚለው።*

*እንደማንኛውም የአናሳ ብሄር ወይም ቡድን ገዢ መደብ፣ ወያኔ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሥልጣኑን ለማንሰራፋት ያለው አንድ ብቸኛ አማራጭ በጉልበት መግዛት ነው። ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር የበላይ ሆኖ እንዲገዛ ስለማይፈቅድለት እንደምንም ብሎ የውሸትም ቢሆን "ካሮትና በትር" እያሳየ በበላይነት መግዛት ነበረበት። እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ቢሆንማ ኖሮ ባገሪቷ ውስጥ ሊኖረው የሚገባ የሥልጣንም ሆነ የምጣኔ ሃብታዊ ድርሻ፣ የቆዳ ስፋትና የህዝብ ብዛትን መሰረት ባደረገው ያገሪቷ ፌዴራሊዝም ህገ መንግሥት መሰረት፣ ወያኔ ሊያስተዳድር የሚችለው ድርሻው ከአስር በመቶ አይበልጥም ነበር። በተግባር የሆነውና የኢትዮጵያን ህዝብ እያናደደ ያለው ዓይን ያወጣ አሰራር ግን፣ በፖሊቲካም ሆነ በምጣኔ ሃብት ይዞትና አስተዳደር ሙሉ በሙሉ የበላይ ተቆጣጣሪና ባለቤት ሆኖ የሚገኘው ወያኔና ባብዛኛው ከትግራይ ብሄር የተውጣጡ በወያኔ ዞርያ የተኮለኮሉና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ በላይ ተጠቃሚ የሆኑ ግለሰቦች መሆናቸው ነው።*

*የመከላከያ ሰራዊቱ የበላይ ሹማምንት፣ በሲቪል የጸጥታና የሚሊታሪ ኢንተሊጀንስ፣ በኢትዮጵያ አየር መንገድና በጉምሩክ እንዲሁም በሌላ ገቢን በሚያስገኙ ወይም የፖሊቲካ ሥልጣንን በሚያጎናጽፉ መስኮች የአስተዳደሩን ቦታ የሚይዙት ትግርኛ ተናጋሪዎች መሆናቸው በገሃድ የሚታይ ዕውኔታ ነው። በየክልሉ የኤኮኖሚውን እንቅስቃሴ በበላይነት የሚመሩትና ባብዛኛው የሚያንቀሳቅሱት የትግራይ ብሄር ተወላጆች ናቸው። በጉሙዝና በኒሻንጉል ወይም በጋምቤላ ክልሎች ውስጥ ያሉትን ረጃጅም ህንጻዎች፣ የዕጣንና ሽምበቆ ማምረቻዎች፣ የወርቅና የዕብነ በረድ ማምረቻዎችን በሙሉ በባለቤትነት የያዙት የትግራይ ተወላጆች እንጂ የክልሉ ህዝቦች አይደሉም፥ በነቀምቴ ወይም ኢጋር፣ በሃዋሳ ወይም በጂማ የሚገኙትን ነፍስ ያላቸውን የንግድ እንቅስቃሴዎች በባለቤትነት የያዙት ከትግራይ ብሄር የተወለዱና ይባስ ብሎም ባካባቢው ይኖሩ ያልነበሩ አዲስ መጪዎች ናቸው። እንደሚታመነው ከሆነ እነዚህ የትግራይ ብሄር ተወላጆች ይህን ሁሉ ሀብት እንዲያፈሩ የተደረገው ሥርዓቱ ሆን ብሎ እነሱን ለመጥቀም ያሰናዳም ባይሆን፣ በአሰራር ላይ በየመሥርያ ቤቱ ያሉት ትግርኛ ተናጋሪ ባለሥልጣናት "ባገር ልጅነት መንፈስ" ለሌላኛው ትግርኛ ተናጋሪ የሃብት ማግኛና ማካበቻውን መንገድ ስለሚያበጃጁላቸው መሆኑን ህዝቡ ያወቀው ጉዳይ ነው።*

*ሌላው ሆን ተብሎ በግልጽ የሚደረገው "አድልያአዊ" አሰራር ደግሞ የወያኔ መንግሥት ሆን ብሎ በየመሥርያ ቤቱ "በስውር" በከፍተኛው ሹመት ወንበር ላይ ሳይሆን "በምክትልነት" ወይም "በአማካሪነት" ከሥር የሚሸጉጣቸው በተግባር ግን፣ የመሥርያ ቤቱን ሥራ በተመለከተ ብቸኛና ወሳኝ የሆኑትን የትግራይ ግለሰቦችን መመደቡን ነው። አንድ በግሌ ያየሁት፣ ዘወትር የሚገርመኝና ከላይ ያሰፈርኩትን ግምቴን በመረጃ ለማስረዳት የሚያመቸኝ ገጠመኝን ባካፍላችሁ ዕውኔታውን ትረዳላችሁ ብዬ እገምታለሁ።*

የሆነው እንደዚህ ነው፣ ባንድ የአፍሪካ ሃገር ለሥራ ተመድቤ ሄድኩና በሆነ ግብዣ ላይ ከኢትዮጵያ አምባሳደር ጋር ተዋወቅሁ። በኦሮምኛ አነጋገሮች ሞቅ ያለ ወሬ ጀመርን፣ በሂደትም የጉሙዝ ሰው እንደሆንና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን የጨረሰው እኔ በተማርኩበት ትምህርት ቤት እንደሆነና በክልል ጎረቤትነት የተነሳ ኦሮምኛን አቀላጥፎ እንደሚችል ነገረኝ። ወዳጅነታችን ቀጥሎ ቡና መገባበዝ ጀምረን የኢትዮጵያንም ፖሊቲካ በግልፅ ማውራት ጀመርን፣ ባጭሩ፣ "ምንም እንኳ ኢህአዴግ የጉሙዝና ቤኒሻንጉልን ህዝብ ከነበረበት የጨለማ ህይወት አውጥቶ ዛሬ ያለንበት ደረጃ ላይ ማድረሱ የሚያስመሰግነው ቢሆንም፣ መሬቱን ከለለው "አስተዳድሩት" ተባልን እንጂ በተግባር የክልላችን ገዢዎች ትግርኛ ተናጋሪዎች ናቸው፣ በዋና ከተማዋ አሶሳ የሚገኙትን ህንጻዎችና በክልሉ የሚገኙትን የዕጣንና የሽምበቆ፣ የማንጎና የጥጥ እርሻዎች ባለቤት ትግርኛ ተናጋሪዎች ናቸው፥ ደረጃው ከፍ ያለ አይሮፕላን ማረፍያና ሰባት ድልድዮችን በአባይ ወንዝ ላይ መዘርጋታቸው ወንዙ ለሁለት የከፈላቸውን የጉሙዝና ቤኒሻንጉል ህዝቦችን ለማገናኘት ታስቦ ሳይሆን፣ ራሳቸው በቀሰቀሱት በኦሮሞዎችና በኛ ህዝቦች መካከል በተፈጠረው ግጭት ምክንያት በግምቢ በኩል ወደ አዲስ አበባ መሄድ ስላልተቻለ ከክልላችን የሚዘርፉትን ወርቅና ዕብነበረድ በጎጃም በኩል ለማመላለስ እንዲያመቻቸው ታስቦ ነው" አለኝ። ይገረምህና ብሎ ቀጠለ፣ "እዚህ አሁን አምባሳደር ተብዬ ተሾምኩ እንጂ የኢምባሲውን ሥራ ሙሉ በሙሉ የሚያካሄደውና የሚመራው፣ ያውም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሳይሆን ከደህንነት መሥርያ ቤት የተመደበው ትግርኛ ተናጋሪ ግለሰብ ነው" አለኝ። "የኤምባሲው ሠራተኞች በሙሉ እኔን ጨምሮ ለሥራ ጉዳይ ስልክ ለመደወል በቅድሚያ እሱ ጋ ማስመዝገብ አለብን፣ እሱ ግን ማስመዝገብ የለበትም፣ የደህንነት ሥራ ነው ተብሎ" ወደ ፈለገበት አገር በፈለገበት ሰዓት ለመደወል ይችላል" አለና ምሬቱን አካፈለኝ።

ሌላው እንደው የወያኔ መንግሥት የትግራይን ሰፊ ህዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ሆን ብሎ ለማጋጨትና፣ እነሱም ህዝቡን፣ ህዝቡም ደግሞ እነሱን በጠላትነት እንዲፈርጅ በማሰብ ለትግርኛ ተናጋሪ ኤሊቶች ብቻ የሚያደርገው ልዩ ጥበቃና ጥንቃቄ ነው። በአንድ የምዕራብ ወለጋ ከተማ አንድ በጣም ትዕቢተኛ የትግራይ ነጋዴ በየቡና ቤቱ ሲሞላፈጥ የተናገሩትን የከተማውን ታዳጊ ኦሮሞ ነጋዴ በሙሉ የኦነግ ደጋፊ ናቸው ብሎ በገፍ ሲያሳስር፣ ህዝቡ በቁጣ ገንፍሎ ሱቁ ድረስ ወጥቶ ተቃውሞውን ሲያሰማ ክላሽኒኮቩን ይዞ ወጥቶ መተኮስ ቢጀምርም መቋቋም ሳይችል ቀርቶ ሱቁ ሲዘረፍ ደርዘን ጠብመንጃዎች ተገኙ። ክላሽኒኮቹ ራሱን ከነዋሪው ህዝቦች እንዲከላከልበት "መንግሥት" የሰጠው መሆኑ ነው። በቅርቡም በበደሌ ከተማ በአማራና በኦሮሞ ህዝቦች መካከል ወያኔ ሆን ብሎ በቀሰቀሰውና፣ ለድርጊቱ ተዓማኒነት ለመስጠት በኢኤንኤን እና ዛሚ ሬዲዮ በኩል እንደሰበር ዜና አቅርቦት በነበረው "ግጭት" ወቅት፣ ያካባቢው ህዝብ እንደው በጥርጣሬ አንዱን የትግራይ ተወላጅ ነጋዴ በቁጥጥር ሥር ካዋሉ በኋላ መኖርያ ቤቱ ሲፈተሽ አስራ ስድስት ክላሽኒኮቭ ተደብቆ መገኘቱ ወያኔ ምን ያህል ትግራይ ያልሆነውን ህዝብ እንደማያምንና የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም የሚችለው በጉልበት ብቻ መሆኑንና ለዚህም ደግሞ ለተወሰኑና ታማኝ ለሆኑ የትግራይ ተወላጆች "ልዩ ጥቅም" በመስጠት ህዝቡ እንዲጠላቸው በማድረግ፣ በዚህም ምክንያት የማያወላውል ታማኝነትን ከተጠቃሚው የትግራይ ኤሊት ብቻ ሳይሆን፣ ሰፊውንም የትግራይ ህዝብ፣ በትግሬነታቸው ብቻ የሌላው ብሄር ህዝብ እንደሚጠላቸውና ወያኔ ከሌለ የመኖር ዋስትና እንደሌላቸው አድርጎ በማቅረብ ነው።

በርግጥ እነዚህ "መንግሥት" በፖሊቲካውም ሆነ በንግዱ ዘርፍ የበላይነትን ያስጎናጸፋቸው የትግራይ ተወላጅ "ባለጊዜዎች" በየመሥርያ ቤቱና በየንግድ ማዕከላቸው የሚያሳዩትን ዕብሪት ያየ ሰው ከነዚህ "ህዝቦች" ጋር አብሮ ለመኖር የሚቻል አይመስለውም። በአንድ መሥርያ ቤት ካለው የመምርያ ሃላፊ ይልቅ ታች ያለችው ትግርኛ ተናጋሪ ጸሃፊ የበለጠ በራስ የመተማመን ሁኔታ የምታሳይበት፣ ካንድ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ውሳኔ ይልቅ የአንድ ትግርኛ ተናጋሪ የወህኒ ቤት አዛዥ ውሳኔ የበላይነት ሲኖረው፣ በየክልሉ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩት ትግርኛ ተናጋሪ "ልማታዊ ባለ ሃብቶች" የሚያሳዩት ዕብሪት በጣም የሚያቅለሸልሽ ደረጃ ላይ በመድረሱ፣ ህዝቡ በደፈናው በትግርኛ ተናጋሪው ህዝብ ላይ አንድ የጋራ የሆነ የጥላቻ አቋም የወሰደ ይመስላል። ልጆቹ ተምረው ሥራ ሲያጡና ኑሮ ከብዷቸው ወላጆቻቸው ቤት ተመልሰው ለመኖር ሲገደዱ የኦነግ ወይም የግንቦት ሰባት አባላት ወይንም ደግሞ ብሎጌር ናችሁ ተብለው ወህኒ ቤት ሲወረወሩ፣ ይህን ግፍ ደግሞ ላለመቀበልና ባገሬም ሰላማዊ ኑሮ መኖር ካልቻልኩ የፈለገው ይምጣና በረሃ ውስጥም ቢሆን ልሙት ብሎ ወጣቱ በገፍ ሲሰደድና፣ በአስራ አንድ በመቶ አድንአል ተብሎ የሚወራለትን የኤኮኖሚ ዕድገት ተጠቃሚው ጥቂት የሥርዓቱ ደጋፊ መሆናቸውን ሲያስተውል፣ በፖሊቲካ ምክንያት ከሚታሰሩትም ሆነ በገፍ ከሚሰደዱት ወጣቶች መካከል አንድም የትግራይ ብሄር ተወላጅ አለመኖሩ፣ ሥርዓቱ በርግጥም ለትግርኛ ተናጋሪዎች የተመቻቸ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ እንድንደርስ ያስገድዳል። ሌላው ቢቀር፣ ኦነግና ግንቦት ሰባት በሽብርተኝነት ሲፈረጁ፣ ከነሱ እጅግ በጣም በላቀ መልኩ የተደራጀና የታጠቀ **"የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ወይም ቲፒዲኤም"** እዚያው አስመራ የሚገኝና በኢሳይያስ የሚደገፍ የሽምቅ ተዋጊ ድርጅት በሽብርተኝነት ከመፈረጅ ያዳነው የትግራይ ተወላጆች ድርጅት በመሆኑ ብቻ እንደሆነ ህዝቡ እያስተዋለው ነው።

እነዚህ እንግዲህ ወያኔ በመንግሥት ስም ከሚፈጽማቸው፣ የትግራይን ኤሊትና ደጋፊውን ለመጥቀምና በሌሎች ብሄር ተወላጆች ላይ ያደረገው ጫና አመላካች የሆኑትን አንዳንድ ድርጊቶችን ለአብነት ያህል አነሳኋቸው እንጂ የሚደረገውን በሙሉ በጽሁፍ ማስቀመጥ ኢንሳይክሎፔድያ ሊወጣው ስለሚችል፣ አለመሞከሩ ይመረጣል። ያ በእንዲህ እንዳለ፣ ወያኔ የትግራይን ህዝብ አይወክልም፣ የትግራይ ሰፊ ህዝብም ደግሞ ከወያኔ አንዳችም ዓይነት ልዩ ጥቅም ስላላገኘ፣ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች እኩል የተበደለ ለመሆኑ አመላካች ናቸው ብዬ የማስባቸውን ጥቂቶቹን ብቻ ላነሳ እሻለሁ።

**ሀ**) የትግራይ ህዝብ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ህዝብ ክፉም ደግም ያለበት ማህበረሰብ ነው። ደጋጎች ያሉበትን ያህል አልፎ አልፎ ክፉዎችም ይኖሩበታል፣ ማህበረሰቡን በጥልቅ ባላውቅም ወያኔ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ለሥራ ጉዳይ ካንዴም ሁለቴ መቀሌን፣ አድዋን፣ ሽሬንና አክሱምን በጎበኘሁበት ጊዜ ከሴቶቹ የጸጉር አሰራርና በየቡና ቤቶቹ በሙሉ ከሚሰማው የትግርኛ ሙዚቃ በስተቀር በአስተሳሰባቸው፣ በአነጋገራቸውና በአቀራረባቸው ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚለዩበትን ነገር አላስተዋልኩም። ለሥራ ጉዳይ ሽሬና እንዳሥላሴ የተመደቡት የመሃል አገር የሥራ ባልደረቦቼም እነደነገሩኝ ከሆነ አንዳንድ ጊዜ በከተማይቷ ውሃ ሲጠፋ የማይተዋወቋቸው ጎረቤቶቻቸው ሌሊት ሌሊት ያላንዳች መሰልቸትና ማቋረጥ ንጹህ ውሃ በባልዲ ቀድተው ደጃቸው ላይ እንደሚያኖሩላቸውና በምላሹ ግን ምንም ዓይነት ጥቅም እንደማይጠብቁ በአግራሞት ነግረውኛል። ጨምረውም፣ እነዚህ ወደ መሃል አገር ድረስ የዘለቁት ወያኔና ጥቂት የጥቅም ተካፋዮቻቸው በማህበረሰቡ ውስጥ በግብረ ገብና በሌላ ሌላም ጠባያቸው ያልተወደዱና ማህበረሰቡ ገፍቶ ያስወጣቸው ዝቃጮች ሳይሆኑ አይቀርም ብለው አጫውተውኛል። መሃል አገር ያሉት የወያኔ ኤሊቶችና ጀሌዎቻቸው ጠባይ ከሰፊው የትግራይ ህዝብ ጋር አንዳችም ዓይነት ተመሳሳይነት የላቸውም ማለታቸው ነው።

**ለ**) ከትግራይ ጓደኞቻችን በተለይም ወያኔን ከሚጠሉት የትግራይ ተወላጆች እንደምንሰማውና በተግባርም ካዩት እንደተረዳነው፣ የትግራይ ህዝብን የሰው ልጆች መብት ጥበቃን በተመለከተ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝቦች የተለየ አንዳችም የተሻለ ማዳላት አይታይም። ወያኔ ቀሪውን የኢትዮጵያን ህዝብ መብት ረግጦ የሚገዛውን ያህል የትግራይ ሰፊ ህዝብንም እየገዛ ነው። ከታመኑት ምንጮች እንደምንሰማውም፣ በትግራይ ክልል የሰፈነው የመልካም አስተዳደር እጥረትና የሙስና መፋፋት በማንኛውም መልኩ ከሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች ከሚታየው የከፋ እንደሆነ ይጠቁማሉ። በመሃል አገር ህዝቡ በእምቢተኝነት ወጥቶ ድምጹን ሲያሰማ በትግራይ ክልል ግን እንኳን የተቃውሞ ሰልፍ ማሰማት ይቅርና ለመደበኛ ስብሰባም የወያኔ ባለሥልጣናት ፈቃድ ያስፈልጋል። ተምሮ ሥራ የሚያጣው ወጣት ቁጥር እጅግ በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደደረሰ ታዛቢዎች ገምተዋል። የህዝቡ የመደህየት ደረጃ የዛሬ ሃምሳ ወይም ስድሳ ዓመት ከነበረው የከፋ እንጂ ያልተሻለ በመሆኑ በጣም ብዙ ሰዎች ወደ መሃል አገር ሄደው በልመና እንዲሰማሩ ቢገደዱም፣ ወያኔ በግድ ወደ ትግራይ እንደሚመልሳቸው የታወቀ ነው።

**ሐ**) ብዙዎቻችን እንግዲህ የጥቂት እፍኝ የማይሞሉ፣ ከትግራይ ህዝብ አንዳችም ዓይነት ውክልና የሌላቸውን እነ መለስንና አቦይ ፀሃይን የመሳሰሉ የፖሊቲካ ደናቁርት፣ ለግል ሥልጣናቸው ብቻ የቆሙና በዚያ ሥልጣን ወንበር ላይ ለመቆየት ደግሞ የተቃወማቸውን ዜጋ በሙሉ ከማሰር፣ ከማሰቃየትና ከመግደል የማይመለሱ አውሬዎች ከሚፈጽሙት እኩይ ተግባር ተነስተን የትግራይን ህዝብ የወያኔ ደጋፊና የሥርዓቱ ተጠቃሚ አድርገን ማየታችን ትክክል አይመስለኝም። ድሮ በፊውዳሉ ዘመን የሰሜን ወገኖቻችንና የተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሳይቀር ወደ ደቡብ እየመጡ ህዝቡን ከነዛ መሬቱ እያፈናቀሉ ለገባርነት ያደርጉ በነበረበት ዘመን በተማሪው ማህበር ውስጥ የነበረው እልህ አስጨራሹ የመከራከርያ ነጥብ የፊውዳል ሥርዓቱ ተጠቃሚ የነበሩትን ግለሰብ ነፍጠኞች፣ አስተዳዳሪዎችና ባላባቶችን ከሰፊው የአማርኛ ተናጋሪ ህዝብ መለየቱ ነበር። የትግራይ ህዝብ ኢትዮጵያን ባህር አልባ ያረጋትን የፖሊቲካ ደንቆሮውን መለስ ዜናዊን ያፈራውን ያህል፣ የኢትዮጵያን ልዕልና ይፈታተኑ የነበሩትን የጎረቤት አገሮችን በቆራጥነት ይዋጉ የነበሩትን እነ አሉላ አባ ነጋን፣ ወይም ደግሞ የጣሊያንን አገዛዝ አልቀበልም ብሎ ላገሩ ያለውን ታማኝነት በህይወቱ የከፈለውን ዘርዓይ ደረስን፣ ወይም ደግሞ በመዲናችን በጄኔራል ግራዚያኒ ላይ ቦምብ የወረወሩና ኋላ ላይ የተገደሉ አገር ወዳድ ትግርኛ ተናጋሪ ጀግኖቻችን አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶምን ያፈራ ታላቅ ህዝብ ስለሆነ፣ ወያኔዎች ዛሬ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በሚፈጽሙት ግፍ ተንገሽግሸን የትግራይን ሰፊ ህዝብና ወያኔን አንድ ላይ ከመውቀጥ ከባድ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን ባይ ነኝ። ሥርአትና ህዝብን መለየት አለብን ማለቴ ነው።

**መ**) ወያኔን ከትግራይ ሰፊ ህዝብ ለይተን ማየት ካልቻልንና "እነዚህ ትግሬዎች" በማለት የጅምላ ፍረጃ ላይ ካተኮርን መዘዙ እጅግ በጣም አስከፊ ይሆናል። በመጀመርያ ደረጃ፣ ወያኔ የትግራይን ህዝብ "ድሮም ብያችሁ ነበር እኮ፣ እኔ ከለሌሁ ቀሪው ህዝብ ይጨርሳችኋል ብዬ" በማለት የማይደግፈውን የትግራይን ህዝብ ሳይቀር ሳይወዱ በግድ ከኋላው ሊያሰልፍና የግፍ አገዛዝ ዕድሜውን ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ሊያራዝም ይችላል። ድሮም በጥርጣሬ ዓይን ይመለከታቸው የነበረው ቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ፣ እውነትም እነዚህ ህዝቦች ወያኔን ይደግፋሉ በማለት የጥላቻቸውን ደረጃ ከፍ ያደርጋሉ፣ እዚያ ደረጃ ከተደረሰ አሁን እያቆበቆቡ ያሉት ዛሚ ሬድዮና ኢኤንኤን የተባለው "የግል" የቴሌቪዥን ጣቢያ ህዝቡን ለማጫረሻ የሚረዳ በቀላሉ ጥሩ የሽቀጥ መጠቅለያ አገኙ ማለት ነው። ያ ነው አደጋው!

**ሠ**) በብዙ አገራት እንደተስተዋለው፣ አናሳ ብሄረሰቦች ወይም ቡድኖች፣ ባንድ የታሪክ ወቅት ሥልጣን ከያዙ በኋላ፣ ኢጋጣሚ የቸረቻቸውን ዕድል ላለማጣትና ተደላድሎ ለመግዛት፣ ህዝቡን በተቻለ መጠን ከፋፍሎ መግዛት እንዳለባቸው ያስተዋልነው ነው። ዲሞክራሲያዊ አሰራርን ከተጠቀሙ አናሳነታቸው ስለሚያስጠቃቸው የበላይነትን እንጂ እኩልነትን አይቀበሉም። ሥልጣን ላይ የወጡት ደግሞ ከህዝባቸው ምንም ዓይነት ውክልና ሳይሰጣቸው ቢሆንም፣ በሂደት ውስጥ ተገዢው ህዝብ በድርጊታቸው ተንገፍግፎ ለምሳሌ፣ ወያኔና የትግራይ ህዝብን ነጥሎ ማየት ተስኖት አንድ ላይ ሲፈርጃቸው፣ "የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ ስለሚጠላን የትግራይ ህዝብ ተባብረን ከነዚህ በጅምላ ከሚጠሉን በመከላከል ህልውናችንን ማስከበር አለብን" በማለትና የዋሁን የትግራይን ሰፊ ህዝብና ቀሪውን የኢትዮጵያን ህዝብ ለርስ በርስ ጦርነት መጋበዛቸው አይቀሬ ይመስለኛል።

***ታዲያ ምን ማድረግ አለብን?***

*ለፖሊቲካ ጥያቄ ሂሳባዊ ፎርሙላ ስለሌለው፣ በርግጠኝነት አንዳች ዓይነት መፍትሄ ማቅረብ ባልችልም፣ እንደው ከልምድ ተነስቼ  የሚከተለውን ለማለት እሻለሁ። ለኔ መልሱ ቀላል መስሎ  ቢታየኝም ለብዙዎቻችን ግን ላይዋጥ የሚችል እንደሆነ ከወድሁ እገምታለሁ። ግን ደግሞ፣ አሁን ያለው ቀውስ ከቀጠለና፣ ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማጫረስ ዝግጁ መሆኑን ካመንንበት አንዳች ነገር ማደረግ አለብን እላለሁ፣ በኔ ግምት ሊደረጉ የሚገባቸው የሚከተሉት ሲሆኑ፣ በጉዳዩ ያገባናል፣ እንቆረቆራለን የምንል ባለድርሻ አካላት ደግሞ በያለንበት በመንቀሳቀስ ቀጥዬ ከማስቀምጣቸው ተግባሮች መሃል እንደየአቅማችን የሚመቸንና ማድረግ የምንችለውን በመምረጥ የየበኩላችንን ማዋጣት አለብን ባይ ነኝ።*

*በመጀመርያ ደረጃ ወያኔ የትግራይ ህዝብ ተወካይ እንዳልሆነ ተገንዝበን ህዝብና ወያኔን መለየት አለብን፥ የምንቃወመው ወያኔ የሚያራምደውን ሥርዓት እንጂ የትግራይን ህዝብ አለመሆንኑን ለራሳችን ብቻ አምነን መቀበል ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ማሳመን አለብን። የምንዋጋው የገዠውን ሥርዓት እንጂ አንድን ህዝብ እንዳልሆነ በጥልቁ መማርና ማስተማር አለብን። ለዚህ ደግሞ ትልቁን ሚና ሊጫወቱ የሚችሉና ታሪካዊ ኃላፊነት ያለባቸው የሚዲያ አካላት ናቸው። የሚጽፉት የሚናገሩትና የሚያሳዩት ምስል ትልቅ አስተዋጽዖ እንዳለው በመረዳት ተግተው በህዝቦች መካከል አንዳችም ዓይነት ቅራኔ እንዳይፈጠርና <u>ተባብረው</u> ወያኔን እንዲወጉ ለሰላማዊው ህዝባዊ አመጽና እምቢተኝነት ህዝቡን ማነሳሳት አለባቸው ባይ ነኝ ።*

*ከዚህ በፊት ደጋግሜ እንዳልኩትና አሁንም ያለመታከት የምደግመው፣ አሁን ካለንበት ቀውስ ለመውጣትና አገሪቷን ከተጋረጠባት አደጋ ለማዳን፣ ከዚሁ ከሚገድለን፣ ከሚያስረንና ከሚያሰቃየን አረመኔ ወያኔ ጋር ሥልጣንን በእኩልነት ለመጋራት መደራደር አለብን። አውቃለሁ ይህ አባባሌ ለብዙዎቻችን የማይዋጥ መራራ ኮሶ እንደሆነ። ግን ደግሞ አንድ ብሩህ መምህር እንዳሉት ከስኳርና ከኮሶ ቢያማርጡን ሁላችንም በርግጥ ስኳርን ነው የምንመርጠው፣ ይጣፍጣልና። ግን መዘዙ መራራ ሊሆን ይችላል፣ ስኳር ሆድ ውስጥ ያለውን ወስፋት ያፋፋልና። ኮሶ ግን ሲጠጣ ይመራል፣ ግን ያሽራል፣ ሰውነትን ከበሽታ ያድናል። ስለዚህ እየመረረንም ቢሆን ኮሶውን ብንጠጣ ይሻላል ባይ ነኝ። ሌላ አማራጭ ቢኖረን፣ ለምሳሌ ስንጠጣም እየጣፈጠን የሚያሽር መድኃኒት ቢኖር ኖሮ ያንን በወሰድን ነበር፣ ያ ዓይነት መድኃኒት ደግሞ ለጊዜው የለንም። መድኃኒቱ ለወደፊት እስኪፈለሰፍ ወይም ከውጭ አገር ተጭኖ እስኪመጣ ድረስ ደግሞ ህዝቡ በበሽታው አልቆ መድሃኒቱ በሚደርስበት ሰዓት ታካሚ ስለማይገኝ ተፈለጊነት ይኖረውም። ስለዚህ ዛሬ በጃችን ላይ ያለውን መራራውን ኮሶ እንጠጣ፣ እየበደለንና እየገደለን ካለው ከወያኔ ጋር ሥልጣንን በእኩልነት ለመጋራትና የዲሞክራሲያዊቷን ኢትዮጵያን መሰረት በጋራ ለመገንባት እንደራደር ባይ ነኝ።*

*ወያኔ በጣም የተደራጀና የጭቆና አውታሩን በሰፊው የዘረጋ መንግሥት ነው። የመከላከያ ሠራዊቱና የደህንነት መዋቅሩ በጣም የጠነከረና ማንኛውንም ዓይነት ጥቃት ለመከላከል የተዘጋጀ ነው። ግን ደግሞ እንደማንኛውም መንግሥትና ሥርዓት ሰው እንኳ ባይገፋው ራሱ በራሱ በስብሶ አንድ ቀን መሞቱ አይቀርም፣ ችግሩ ግን ያ የመሞቻው ቀን እስኪደርስ ድረስ የብዙ ዜጎቻችንን ነፍስ ሊያጠፋ ይችላል። ስለዚህ ዲያሌክቲካዊ ሂደትን ተከትሎ ራሱ እስኪሞት ድረስ መጠበቁ ስለማያዋጣ፣ የዚህን ሥርዓት ዕድሜ ማሳጠር አለብን። አዎ ወያኔ ለጊዜው ጠንካራ ድርጅት ነው፣ ግን ደግሞ በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ፣ ከተባበረ የህዝብ ክንድ በላይ የሚጠነክር ኃይል ሊኖር አይችልም። ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝቦች አሁን እንደምናየው በተናጠል ሳይሆን በጋራ <u>አንድ ላይ ባንድ ጊዜ</u> ተነስቶ በእምቢተኝነት ቢቀጥልበት ወያኔን ወደ ድርድር ጠረጴዛ መጥቶ ሥልጣንን በእኩልነት ለመጋራት እንዲደራደር ልናስገድደው እንችላለንና ለዚያ እንትጋ ባይ ነኝ። በቸር ይግጠመን።*

**********

*ጄኔቫ ፌብርዋሪ 5 ቀን 2018 ዓ/ም*
wakwoya2016@gmail.com